# ***ቅንዓት***

*ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ*

*ቅንዓት ምንድን ነው? እንዴትስ ይገለጣል? «ከሴት ከተወለዱት የሚያህለው የለም» ብሎ ጌታችን የመሰከረለት መጥምቁ ዮሐንስ በቅንዓትና በድፍረት እውነትን መግለፁን እንደ ዋና ምሳሌ አድርገን በመውሰድ ስለቅንዓት እንማራለን፡፡ «የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፡፡» መዝ 69፡9፡፡ ተጨማሪ **ሉቃስ 7፡28-35፣ ነህ.2፤ ያዕ.3፡13-17፡፡***

*ቅንዓት ሰው በቅንነት መልካም ነው ብሎ ያመነውን በራሱ ፈቃድ ከልቡ በማመንጨት አሊያም ከእግዚአብሔር ፈቃድ በሆነ ኃይል አማካይነት ሲታዘዝ ለነገሮች የሚያሳየው ወገንተኝነት ነው፡፡ አንድ ሰው ትክክለኛ ለሆነ ነገር በመንፈሳዊነት ትክክለኛ ላልሆነ ነገር በስሜት ሊቀና  ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለ ቅንዓት ብትጠየቁ ቤተክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርሁ፡፡» ፊል. 3፡6 ያለው፡፡ በማለት ትክክለኛ ያልነበረውን ቅንዓቱን አስልክቶ የጻፈልን፡፡*

*መዝሙረኛው ዳዊት «የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፡፡» እንዳለው የሆነ የተቀደሰ ቅንዓት አለ፡፡ ከዚህ በተቃራኒም በገላ 5፡20 በሥጋ ሥራዎች እንደተገለጠውና መዝሙረኛው ንጉሥ «ቅንዓት እንደ ሲኦል የጨከነች ናትና» **መዝ. 8፡6** በማለት የዘመረበት ዓይነት ክፉ ቅንዓት ወይም ከኃጢአት የሆነ ቅንዓትም አለ፡፡ ክርስቲያኖች ግን «ሁልጊዜ በመልካም ነገር ተፈላጊ ብትሆኑ መልካም ነው፡፡» **ገላ.4፡18**፡፡ በተባልነው ምክር ብቻ በመመራት በመንፈሳዊ ቅንዓት ልንኖር ይገባል፡፡*

*በጭፍን፣ በስሜት፣ ያዕውቀትና ሳያጣራ፣ በነገሮችም እርግጠኛም ሳይሆን በሰማው ነገር ብቻ ተመርቶ የሚቀናም ሰው አለ፡፡ ይህም መልካም ያልሆነ ቅንዓት ነው፡፡ ሐዋርያው «በዕውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና፡፡» ሮሜ 10፡2፡፡ ብሎ የቅንዓትን ቦታውን አሳይቶ መልካም ስላልሆነው የአይሁድ ቅንዓት ነግሮናል፡፡ ጌታችን «የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ወራት ይመጣል፡፡» ዮሐ 16፡2 እንዳለው ይህ ቅንዓት ከእውነት የተለየና የተርሴሱ ሐዋርያ «ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ...፡፡» 1ኛ ጢሞ.1፡13፡፡ በማለት የገለጠው ዓይነት ወደ ጸጸት የሚያደርስ ቅንዓት ነው፡፡ ስለዚህም በችኮላ አትቅና፡ ቅንዓትህን በዕውቀት አድርገው እንጂ! ስለሌሎች የሚነገርህን ሁሉ አትመን! በተሰጠህ አእምሮ አስበህ፣ አጥንተህና አረጋግጠህ መልካሙን ባሕርይ ተከተል!*

*ቅዱስ ጴጥሮስ ለጌታችን ቀንቶ የባርያው የማልኮስን ጆሮ መቁረጡ፤ በተጨማሪም ዮሐንስና ያዕቆብ የሰማርያ ሰዎች ጌታችንን ስላልተቀበሉት እሳት ከሰማይ ወርዶ ይብላቸው ያሉበት ቅንዓት በአምላካችን ያልተደገፈ ነበር፡፡ ሉቃ9፡54፡፡ በመሳደብና ስም በማጥፋት ወይም የሰው ልብ በመጉዳትና በማሳፈር ወይም በአመጽና በማፍረስ ሥጋዊ ቅንዓት የተሞሉና ሰውን በእነዚህ ጥፋቶች የሚጥሉ አንዳንዶች ደግሞ አሉ፡፡ እነኚህ ሰዎች ለጥፋትና በጎ ነገርንም ሁሉ ለማፍረስ መሣሪያ የሆኑ፣ ለራሳቸውና ለባልንጀሮቻቸው ጥብቅና የቆሙ ሲሆኑ ድርጊታቸውም በማንኛውም መመዘኛ ተቀባይነት የሌለውና ከመንፈሳዊነት የወጣ ነው፡፡ እነዚህም በሐዋርያት ሥራ የተጠቀሱትን ቅዱስ ጳውሎስን ሳይገድሉ ምግብ እንደማይበሉ በመማማል ለእግዚአብሔር መቅናታቸው ለመግለጽ ሞክረው የነበሩትን አርባ የሚሆኑትን አይሁድን የሚመስሉ ናቸው፡፡ **የሐዋ 23፡12፡፡** ይህን የሚፈጽሙም መንፈሳዊ ዕውቀት ጎድሎአቸዋልና እንዲህ ያለው ቅንዓት በመንፈሳዊ ዕውቀት ያልተደገፈና በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡*

*ከራስ ወዳድነት እና ከተዛባ መረጃ የሚነሳ ቅንዓትም አለ፡፡ ኢያሱ ስለ ሙሴ ቀንቶ በሰፈር ትንቢት የተናገሩትን ሲቃወም ሙሴ «የእግዚኣብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ፤ እግዚኣብሔርም መንፈሱን ቢያወርድ አንተ ስለኔ ትቀናለህን?» እንዳለው፡፡ **ዘኁ.11፡2፡፡***

*ታዲያ አሁን በዙሪያችን የምንመለከተውስ ቅንዓት ምን ዓይነት ነው?*

*በሰኔ 30 ቀን ልደቱን የምናከብርለት መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ በእግዚኣብሔር የተመረጠ፤ ጌታችን አምላካችንም የመሰከረለት ቅዱስና በቀናዒነቱም ለሁላችን አብነት የሚሆነን አባት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች በሌሎች ሰዎች (በቅርብ ወዳጆቻቸው) ታላቅ ይባላሉ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ግን «በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፤ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ገናም በናናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስቅዱስ ይሞላበታል፡፡» **ሉቃ. 1፡15** «እውነት እላችኋለሁ፤ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም» **ማቴ.11፡11**፡፡ በማለት እግዚአብሔር የመሰከረለት ቅዱስ ነው፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ቅንዓትን የሚቀና ሰው የሚታወቅበት አንዱ መንገድ በእግዚአብሔርና በቃሉ የሚመሰክርለት መሆኑ ነው፡፡*

ቅዱስ ዮሐንስ ሳይወለድ መንፈስቅዱስ የሞላበት ብቸኛው ሰው ነው፡፡ በተልዕኮው ወይም በአገልግሎቱም ሕዝቡን ወደ አምላካቸው በመመለሱ «የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ ሲያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል፡፡» የተባለለት ነው፡፡ የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ታላቁ ተልዕኮው ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት የእግዚኣብሔር ልጅ የዓለም መድኅን መሆኑን ለዓለም መግለጥ ነበር፡፡ ይህንም በትክክልም ፈጽሞታል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ ተልዕኮውን የፈጸመው በእውነት መንፈስ በመንፈስቅዱስ በመመራት ነው፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ ምሉዕ እውነታዎችን በጠንካራ ቃላት ሲገልጥ የምናነበው፡፡ ለምሳሌ ማነህ? ተብሎ ሲጠየቅ «እኔ ክርስቶስ አይደለሁም» ብሎ ማንነቱን ሳይክድ በትሕትና ጭምር «የጫማውን ጠፈር ልፈታ የማይገባኝ» በማለት ስለጌታችን ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡ <u>ዮሐ. 3:28-36፡፡</u> እውነተኛ ቀናዒ ግማሽ ማንነቱን በመሸፈን ብዙዎችን ሊያሳምንልኝ ይችላል ያለውን ያልተረጋገጠ ጎኑን ሳይሆን እውነተኛ ማንነቱን በመግለጽ በውስጥም በውጭም ለአማንያን ሁሉ ያለ ችግር ይነበባል፡፡

የቅዱሳንና የሰማዕታት ሕይወት ዋነኛው መገለጫ የተቀደሰው ቅንዓታቸው ነው፡፡ የዚህ ቅንዓት ምንጩም በቅዱሳን አድሮ የሚሠራ የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ነው፡፡ የተቀደሰ ቅንዓት በመለኮታዊ ፍቅር የተመሠረተና ከልዩነትና አድሎአዊነት የጸዳም ነው፡፡ ጌታችን በምድር ላይ እሳትን ለመጣል መጣሁ እንዳለ የተቀደሰ ቅንዓት በመለኮት ፍቅር እሳት የተለኮሰ ሲሆን ይኸው ፍቅር ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች መዳን በመቅናት ይገለጻል፡፡ የሚመራውም በመንፈስቅዱስ (በእግዚአብሔር ፈቃድ) እንጂ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ፍላጎት አይደለም፡፡

<u>በማርቆስ 6:17-29</u> እንዳምናነበው መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ በቀናዒነቱ ለእውነት ቀንቶ ንጉሥ ሄሮድስን በመገሠጹ አንገቱን ተቀልቶ የሕይወት አክሊልን ተቀብሎበታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ወንጌልን ለመስበክ፣ ቤተክርስቲያንን ከሐሰተኛ መምህራን ለመጠበቅ የቀናውን ቅንዓት በእንባና በጸሎትም ነበር የፈጸመው፡፡ <u>የሐ.ሥ. 20:17-34፡፡</u>

***ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ልዩነትና መካሠስ ሲገስጽም ለቤተክርስቲያን ከነበረው ቅንዓት ነበር እንጂ ወዳጆቹን ደስ ለማሰኘት ለሥጋ ዓላማውም የሰዎችን የሥጋ ልብ ለመግዛት አልነበረም፡፡*** <u>1ኛ ቆሮ 6:4-8፡፡፡</u>

ከብሉይ ኪዳንም ነህምያ ለኃይለኞች ሳያዳላ ወይም ሰዎችን ሳይፈራ ከቤተመንግሥት የምቾት ኑሮ በላይ ስለ እግዚአብሔር ከተማና ሕዝብ ስለአባቶቹም ርስት ቀንቶ ሲሠራ አይተው የተቃወሙትን «እኔም መልሼ:- የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ባርያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ዕድል ፈንታና መብት መታሰቢያም የላችሁም አልኋቸው፡፡» <u>ነህ 2:20፡፡</u> ብሎአቸዋል፡፡

*ሥጋዊ ቅንዓት ከፍቅር ማጣት፣ ስለእውነት ካለማወቅ፣ ከፉክክርና የራስን ፍላጎት ብቻ ከመከተል የሚመነጭ ሲሆን መገለጫዎቹም ከመንፈሳዊነት የወጡ ናቸው፡፡*

*ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ስለ ቅንዓት ሲያስተምር « ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማነው? በመልካም አነዋዋሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ፡፡ ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ አትመኩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ፡፡ ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም ነገር ግን የምድር ነው የሥጋም ነው፡፡ የአጋንንትም ነው፡፡ ቅንዓትና አድመኝነት ባሉበት ሥፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ አሉና፡፡ ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት በኋላም ታራቂ፣ ገር እሺ ባይ፣ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፣ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት፡፡»* <u>***ያዕ 3:13-17***</u>፡፡ በማለት ***ልንመራበት የሚገባውን ውስጣዊ ሐሳብና መንፈስ እንደነገረን ከስሜት፣ ከማስመሰል፣ የተደበቀ ዓላማንና ፍላጎትን በመንፈሳዊነትና በቀናዒነት ሸፋን (ያለእግዚአብሔር ፈቃድ በግድ) ለመጫን ከመጣደፍ ታቅበን በቃሉና፣ በቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ብቻ!!! እንመራ!***

እንግዲህ የሰዎች ታላቅነትና ቀናዒነት የሚገለጸው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው በሚያከናውኑት የሕይወት ተልዕኮና ውጤታቸው መሆኑን ከማወቅ ጋር እንደ እምነታችን ርቱዕነት የተቀደሰውን ቅንዓት በተግባር በመግለጥ ማሳየት ይጠበቅብናል፡፡ አፍራሽ በሆነው ክፉ ቅንዓት እዳንወድቅም ልንጠነቀቅ ይገባናል፡፡

*አምላካችን እግዚአብሔር ኦርቶዶክሳውያን እንደ መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ሁሌም እውነትን እንድንናገር በመንፈሱ እንዲመራንና በቅዱሳን አሰረ-ፍኖትም እንድንጓዝ ይርዳን፡፡*

**የእግዚአብሔር ፀጋ አይለየን፤ የቅዱስ ዮሐንስ ምልጃም ይደረግልን፡፡**